የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ህዳር ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 8
ADDIS ABABA 15th November, 2004


**ማውጫ**

**CONTENTS**


አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፫/፲፱፻፺፯ዓ.ም

ከኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ.... ገጽ. ፪ሺ፱፻፴፭

Proclamation No. 423/2004

A Proclamation to ratify the Agreement signed on the Reciprocal Promotion and Protection of Investments with the Islamic Republic of Iran Ratification Proclamation…Page. 2935


### አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፫/፲፱፻፺፯

### ከኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ሕጎች መሠረት አስፈላጊ እርምጃዎች ተወስደው በመጨረሻ ላይ አንደኛው ሀገር ለሌላኛው ሀገር ስምምነቱ ሥራ ላይ እንዲውል የሚያስችሉ ተግባራት መከናወናቸውን ካስታወቀ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION NO. 423/2004.

### A Proclamation to ratify the Agreement signed on the Reciprocal Promotion and Protection of Investments with the Islamic Republic of Iran

**WHEREAS**, an Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investments between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Islamic Republic of Iran is signed in Addis Ababa on 21st day of October 2003;

**WHEREAS**, it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the last notification of either country to the other country the fulfillment of the entry in to force measures in accordance with its laws;

**WHEREAS**, the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 28th day of October, 2004;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፳፫/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን በሁለትዮሽ ለማስፋፋትና ጥበቃ ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ፣ ጥቅምት ፲ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል::

**፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ ኃላፊነት ተሰጥቶታል::

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከህዳር ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ከህዳር ፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Reciprocal Promotion and Protection of Investments Agreement with The Islamic Republic of Iran Ratification Proclamation No. 423/2004."

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement on the Reciprocal Promotion and Protection of Investments Signed in Addis Ababa on 21 October 2003 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Islamic Republic of Iran is ratified.

**3. Responsibility of the Ethiopian Investment Commission**

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement this Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force as of the 15th day of November, 2004.

Done at Addis Ababa, this 15th day of November, 2004.

GIRMA WOLDEGIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA